# <u>የዝግጅት ጊዜ ያስፈልጋል</u>!!!

ከባህልቢ ዘማርያም

በሰሜን አፍሪቃ ተቀጣጥሎ የተለያዩ የዓረብ ሀገራትን እያዳረሰ ያለው፤ ዜጎች የዜግነት መብታቸውን ለማስከብር የሚያደርጉትና እያደረጉት ያለው ሰላማዊ ህዝባዊ ንቅናቄና የዜግነት መብታቸው ለማስከበር የከፈሉትና እየከፈሉት ያለው መስዋእትነት የሚደነቅ ነው። በዚህ ህዝባዊ ንቅናቄ ውስጥ የቱኒዚያና የግብጽ የመከላከያ ኃይሎች ያሳዩት ብስለትም የሚደነቅ ብቻ ሳይሆን የሚያስቀናም ነው። የዚህ ዓይነት አርቆ ተመልካች የመከላከያ ኃይል ያፈራ ህዝብና አገር ቢኮራ ይገባልና እንኳን ደስ አላቹህ ሊባሉ ይገባል። በግብጽና ቲኒዚያ ህዝባዊ ንቅናቄው የአምባገነን ሥርዓቱ ቁንጮዎችን አስወግዶ የተወሰነ ምዕራፍ ላይ ደርሷል። በተጠቀሱት አገሮች የተነሳው ህዝባዊ ንቅናቄ የታለመለት ግብ መምታትና አለመምታትን በሚመለከት በሂደት የምናየው ቢሆንም እንዳይቀለበስ ህዝቡ በንቃት ሊጠብቀው የሚገባ ይሆናል።

እነዚህ ህዝባዊ ንቅናቄዎችን ሁላችን በቅርበት እየተከታተልን እያለን አንዳንድ ኢትዮጵያዊያን የዚህ ዓይነት ሰላማዊ ህዝባዊ የእምቢተኝነት ንቅናቄዎች አገራችን ውስጥ ሊከሰቱ ስለሚችሉባቸው ሁኔታዎች ፅፈው በድረ-ገጾች ላይ እያስነበቡን ነው። በዚህ ዙርያ ህዝባዊ አመጹ ምን ሁኔታዎች ላይ ትኵረት መስጠት እንዳለበት ለማሳየት ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ፤ መቶ አለቃ አያልሰው ደሴ፤ አቶ አበበ ገላው፤ ወጣት ጃዋር መሐመድና በቅርቡ ደግሞ ዶ/ር ነገደ ጎበዜ፤ በተለያየ ጊዜ ያወጡዋቸው መጣጥፎች የዚህ ፀሐፊን ቀልብ የሳቡ ናቸው።

እውነት ነው! በኢትዮጵያችን የለውጥ ደወል ካቃጨለ ሰንብቷል። በእውን ለውጥ ካስፈለገንም ዓመታት አልፏል። ሆኖም የለውጥ ደወል በየጊዜው ቢያቃጭልም እኛ ለድሉ ለመድረስ ቀርቶ ለመዘጋጀት እንኳን ሳንችል እንዲሁ ከንፈር እየመጠጥን መክረሙና በስሜት ፈረስ መጋለቡ አልሰለች ያለን ይመስላል። ለውጥን ለማስተናገድ የሚችሉ ምቹ ሁኔታዎች በተፈጠሩ ቁጥር የፀጋዬ ገብረመድኅን አርአያ በአንድ ወቅት በጦቢያ መጽሔት ላይ አስፍሮት የነበረውን ቃል ልዋሰውና "የለውጥ አዋላጆቹ " ራሳቸውን አዘጋጅተው ለመገኘት ሳይችሉ ቀርቷል። ከምር የሚጠበቀውን ሥር ነቀል ለውጥ ለማምጣት ከተፈለገ አቅጣጫ ሊቀይስ የሚችልና ግልጽ ራእይ ያለው የተደራጀ ኃይል ሳይኖለብት የሚጠበቀውን ለውጥ ለማዋለድ የሚቻል አይሆንም። እነዚህ የዘላቂ ለውጥ አዋላጆች በወጉ ተደራጅተው የሚፈለገውን ለውጥ መልክ ለማስያዝና ለመምራት ሳይችሉ የሚከሰት የተናጠል እንቅስቃሴ የባሰ ችግር እንዳያስከትል ጥንቃቄ ሊደረግበት ይገባል።

ይህ በኢትዮጵያ ሊከሰት የሚጠበቀው ህዝባዊ ዓመጽ ምን መልክ መያዝ እንዳለበትና ምን ቅድመ ዝግጅት መደረግ እንዳለበት መቶ አለቃ አያልሰው ደሴ "የህዝባዊ ዓመጽ ራእይ በኢትዮጵያ" (The prospect of popular uprising in Ethiopia) በሚል ርእስ በሶስት ተከታታይ ክፍል ያስነበቡን መጣጥፎች ይህንን ፀሐፊ እጅጉን አርክተውታል። ህዝባዊ ዓመፅ ቢቀሰቀስ አቶ መለስ ያዘጋጁትን የከፋፍለህ ግዛ ፖለቲካ አባዜን በህዝብ መካከል በመንዛት ብሔር ብሔረ-ሰቦችን እርስ በርስ የማባላት ካርድ ሊመዙ እንደሚችሉ፤ ዴሞክራት የአንድነት ኃይሎች በወጉ ሳይሰባሰቡና ህዝባዊ ዓመጹን ባገባቡ ለመምራት ሳይችሉ በተናጠል የሚከሰት የለውጥ እንቅስቃሴ ይበልጥ ሊጠቅም የሚችለው አፍራሽ ኃይሎችን ሊሆን እንደሚችልና እነዚህ አፍራሽ ኃይሎች የአገራችንን አንድነት ሊፈታተኑ እንደሚችሉ፤ ለራሱና ነፃ አወጣሁት ለሚለው ህዝብ ያልሆነን ሻዓቢያ ምርኩዝ አድርገን ኢትዮጵያን እንታደጋለን የሚሉ ኃይሎች የሚከተሉት ጅላጅል ፖለቲካ የኢትዮጵያ አንድነትና

ዘላቂ ሰላሚ ላይ ሊያስከትሉት የሚችሉትን ጣጣ በወጉ አለመገንዘብን የሚያመላክቱና ሌሎችም ያቀረቧቸው ጥልቀት ያላቸው በአመክንዮ የተደገፉ ጠቃሚ ሐሳቦች ይህን ፀሐፊ እጅጉን የተመቹት በመሆኑ መቶ አለቃ አያልሰው ደሴን ባሉበት ምስጋናዬ ይድረስዎ ይላል። ስለሆነም፤ ህዝባዊ ዓመጹን ከራሳችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አያይዘን ሊያጋጥሙን የሚችሉ እንቅፋቶችን ከወዲሁ እያስወገድን እንጓዝ የሚለው አቋማቸው ሊደገፍ የሚገባው ነው ይላል። በመሆኑም ነው ይህ ፀሐፊ የዝግጅትና የትውውቅ ጊዜ ያስፈልገናል ብሎ የሚያምነው። የሚንጠብቀው ለውጥ ካገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በቀጥታ የተያያዘ መሆን ይኖርበታል። ስለዚህም፤ በኛ አገር መካሄድ ያለበት ሰላማዊ ህዝባዊ አመፅ ያገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ በሚገባ ያገናዘበ መሆን አለበት። አገራችን ለ20 ዓመታት ያህል የከፋፍለህ ግዛ ፖለቲካ የተካሄደባት፣ ኢትዮጵያዊነት ደብዝዞ በምትኩ በብሔር ብሔረ-ሰብቦች መብት ስም ጠባብነት እንዲስፋፋ በሕግ ደረጃ አስቀምጦ ተግባራዊ እየሆነባት ያለች አገር በመሆኗ፤ ሰላማዊ ህዝባዊ አመፁ የተለየና እጅግ የረቀቀ ጥበብ የተሞላበት አካሄድ እንዲከተል ያስገድዷል።

አገራችን ውስጥ የነገሠው አምባገነን ኃይል እንዲህ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። አረመኔነቱ ግልጥልጥ ብሎ የወጣና ለመግዛት ካልቻለ ሀገርንም በታትኖ ሊሄድ የሚችል አደገኛ አገዛዝ መሆኑ መዘንጋት የለብንም። ህዝባዊ አመፁ ይህንን ሁሉ ታሳቢ አድርጎ የሚቀረጽ መሆን ይኖርበታል። ሌላው በደንብ ሊታሰብበት የሚገባው ጉዳይ ደግሞ የኢትዮጵያ አንድነትን እንደ ሽፋን በመጠቀም፤ ዛሬ ሥልጣን ላይ የተቆናጠጠው ኃይል የሚያራምደውን የከፋፍለህ ግዛ እኩይ ተግባር ለመድገም የሚቋምጡ ጽንፈኛ አክራሪ ኃይሎችም እንዳሉ ነው። የዚህ አቋም አቀንቃኞች ለመኖራቸው **“የኢትዮጵያ አርበኞች ግንባር”** በሚል ስያሜ በ1994 ዓ.ም.ፈ. በኦክላንደ የተመሠረተ ድርጅት ያወጣውን መርሐ-ግብር (ፕሮግራም) መመልከቱ በቂ ግንዛቤ ይሰጣል። በዚህ ድርጅት መርሐ-ግብር ክፍል ሁለት አንቀጽ 4 ንኡስ ፊደል ሀ. ሥር የሚከተለው ሰፍሮ ይገኛል። **“የኢአግን ዓላማዎች ሙሉ በሙሉ ተቀብሎ ተግባራዊ ለማድረግ ዝግጁ የሆነ፤ ማነኛውም ከትግሬ ጎሳ ያልተዋለደና በጋብቻም ያልተዛመደ ኢትዮጵያዊ፤ እድሜው ከአስራስምንት(18) ዓመት በላይ የሆነ አባል ሊሆን ይችላል።”** ይላል። እንደዚህ ዓይነት አቋም የሚያራምዱና ኢትዮጵያዊ አይደለንም የሚሉ ወገኖችን ሁሉ አግበስብሶ ተሸክሞ አይቀሬውን ህዝባዊ ዓመፅ ሲነሳ የታለመለትን ግብ ማድረስ የሚቻል አይሆንም። ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር የኢትዮጵያ ዴሞክራት ተቃዋሚ ኃይሎች በመካከላቸው ያለውን መለስተኛ ልዩነት ለማጥበብና አብሮ ለመሥራት የሚያስችሉዋቸውን ስትራተጂዎች ከመንደፍ ጀምሮ ማከናወን የሚገባቸው በርካታ ቅድመ ዝግጅቶቻቸውን እንኳን አልጀመሩም። በዚህ ፀሐፊ እምነት ገና የሚጠብቃቸው ዘርፈ ብዙ ውጣ ውረዶች አሉ። ህዝባዊ ዓመፁ አንዴ ከተጀመረ ከንግዲህ በኋላ በድጋሚ መኰላሸት የለበትም። ስለሆነም ህዝባዊ አመጹን በሀገራችን ለመጀመር ለዝግጅትና ትውውቅ በቂ ጊዜ ያስፈልጋል። የኢትዮጵያ ዴሞክራት ኃይሎች የጋራ ግንባር ፈጥረው በጋራ ለመንቀሳቀስ መቻልና አለመቻል የሚነሳውን ህዝባዊ አመፅ ለድል ማብቃትና አለማብቃት ጋር ቀጥተኛ ትስስር እንዳለው በማያወላውል መንገድ መታወቅ አለበት። ለዚህም ነው ዘላቂና ሁለመናዊ ለኢትዮጵያ የሚጠቅም ለውጥ ለማምጣት የዝግጅትና በትክክል መተዋወቅያ ጊዜ ያስፈልጓል የሚባለው። የኢትዮጵያ ዴሞክራቶች ባሰቸኳይ ተሰባስበው ህዝባዊ ትግሉን ለማቀናጀት ባይችሉ አገራችን ሊያጋጥማት የሚችለውን ችግር አስመልክቶ ከላይ የተገለጸው የመቶ አለቃ አያልሰው ደሴ መጣጥፍ በሚገባ የዘረዘረው በመሆኑ፤ ይህ ጸሓፊ ህዝባዊ አመፅ ሲነሳ ሕወሓት/ኢህአዴግ ምን ማድረግ ይችላል በሚለው ላይ አጠር ያለ አስተያየት ለማስፈር ይሞክራል።

ህወሓት/ኢህአዴግ ሰላማዊ ህዝባዊ አመፅ ሲነሳ የሚወስደው አማራጭ ምን ሊሆን ይችላል? የሚለው ጥያቄ በጥልቀት መታየት ያለበት ቁልፍ ጥያቄ ነው። የጠላትን እንቅስቃሴ፣ ስትራቴጂና ታክቲክ ጠንቅቆ ማጥናትና ማወቅ ለህዝባዊ አመፁ በድል መጠናቀቅ ወሳኝነት አለውና። የገጠመን አምባገነን አገዛዝን ከሚገባው በላይ ከፍ አድርጎ ማየት የራሱ አደጋ እንዳለው ሁሉ አሳንሶ መመልከቱም በድልና በውድቀት መካከል ያለ ልዩነት መሆኑ ጠንቅቀን ሊናውቀው ይገባል። የአምባገነኖች ተለዋዋጭ ባሕሪ ግምት ውስጥ በማስገባት የትግሉ ስትራቴጂና ታክቲክ በተለያዩ አቅጣጫዎች እንዲጠና የግድ ይሆናል። በመሆኑም በዚህ መጣጥፍ ውስጥ ህዝባዊ አመጹን ለማክሸፍ የአገዛዙ ዋና መሣርያ ሊሆን የሚችለው የወታደሩ ተራ ምን ሊሆን እንደሚችል አጠር ባለ መልኩ ለማቅረብ ይሞከራል። ውስጥ አዋቂዎች በመረጃዎች አስደግፈው ሰፊ ማብራሪያ እንደሚሰጡን በመተማመን ይህ ፅሐፊ የግሉን እይታ ቀጥሎ ያሰፍራል።

## ያገር መከላከያ ሠራዊት፣

አምባገነኖች ሁሉ ጊዜ ህዝባዊ አመጽን ለመምታት የሚጠቀሙባቸው መሣርያዎችና ዘዴዎቸን ያዘጋጃሉ። ከነዚህም ውስጥ መለዮ ለባሹን (ጦር ኃይልና ፖሊስ)፣ ደኅንነት፣ ለጥቅማቸው ሲሉ የሚፈለፍሏቸው የሲቪክና የሙያ ማኅበራት፣ የመገናኛ ብዙኃን፣ …..ወዘተ የመሳሰሉትን ሙሉ በሙሉ በራሳቸው ቁጥጥር ሥር ማዋል ቀዳሚ ተግባራቸው አድርገው ይወስዳሉ። ባገራችን ተጨባጭ ሁኔታም የአገሪቱ ኢኮኖሚ ከመሬት ይዞታ ጀምሮ እስከ ተራ የችርቻሮ ንግድ ድረስ በገዢው ቡድን መዳፍ ሥር የገባበት ሁኔታ ነው ያለው። እነዚህ ሁሉ የሚቋቋሙትና የሚዋቀሩት የገዢውን ቁንጮዎች ሥልጣን ለመከላከል እንዲያገለግሉ ነው። አገራችን ውስጥ አምባገነኑ ኃይል ሥልጣኑን ለማስጠበቅ ከሚጠቀምባቸው ዋነኛ መሳሪያዎች መካከል የአገር መከላከያ ኃይል በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀስ ነው። በቱኒዚያም ሆነ በግብጽ በተደረጉት ህዝባዊ ንቅናቄዎች የሰራዊቱ ሚና ምን እንደነበረ መላው ዓለም ያየው ነው። ሰራዊቱ የአምባገነኖችን ትእዛዝ ለማስፈጸም ዝግጁ አልነበረም። በተቃራኒ ህዝቡን በመወገን ከተማው ውስጥ የህዝብም ሆነ ግለሰብ ንንብረት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ተከላከሏል። በመሆኑም አምባገነኖቹ በአንጻራዊነት ሲታይ በአነስተኛ የሕያወት ኪሳራ ሊወገዱ እንደቻሉ ታዝበናል።

ስለሆነም፣ በአገራችንም በሰራዊቱ ውስጥ መሰራት ያለበት ስራ በከፍተኛ ደረጃና በቀጣይነት መስራት የግድ ይላል። ያገር መከላከያ ሠራዊትን ከህዝብ ጎን ማሰለፍ ካልተቻለም ገለልተኛ ሆኖ ያገርን ዳር ድንበር የማስከበር ግዴታውን ብቻ በመወጣት ግዳጅ ላይ እንዲሠማራ ማድረግ ለህዝባዊ ንቅናቄው በአሸናፊነት መውጣት ወሳኝነት ባይኖረውም የሚከፈልን መስዋዕትነት እንዲቀንስ ይረዳል። ከዚህም አለፎ የአገር መከላከያ ሠራዊቱ መታረም የሚገባቸው ግድፈቶች እየታረሙ የአገር መከላከያ ሰራዊት ሆኖ እንደሚቀጥል ዋስትና ማግኘት አለበት፣ ከሚመጣው ለውጥ ተጠቃሚ እንደሚሆንም ሊገለጽለት ይገባል። ይህንን በማድረግም ሰራዊቱ የሰላማዊ ህዝባዊ አመጽ አካል ሆኖ ሊቆም ወደሚያስችለው አቋም ለማሸጋገር ይቻላል። በመሆኑም፣ ያገር መከላከያ ሠራዊትና የአገር ደህንነት ሠራተኞች ውስጥ መሠራት ያለበትን የቤት ሥራ ሳይሠራ ህዝባዊ አመፅ መቀስቀሱ የማይፈለግ ኪሳራ እንዳያስከትል ተገቢ ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል። 1997 ዓ.ም. እንደታየው የአገር መከላከያ ሠራዊት የአምባገነኖች መሣርያ ሆኖ ህዝባዊ አመጽን የመጨፍለቅ እርምጃ እንደወሰደው ዛሬም ይህንኑን እንዳይደገም የኢትዮጵያ ዴሞክራቶች ሰራዊቱን የህዝብዊ አመፁ አጋር ለማድረግ ካልተቻለም በገለልተኝነት ቆሞ ዳር ድንበርን ብቻ እንዲከላከል የማድረግ ሥራ በሠራዊቱ ውስጥ በቀጣይነት መሥራት ይጠበቅባቸዋል። ያ የ1997 ዓይነት ሁኔታ ተደግሞ ህዝባዊ አመፁ እንደገና በወታደራዊ ኃይል ከተኰላሸ ሰላማዊ ህዝባዊ አመፅ

አቅጣጫውን ስቶ በሂደት አገሪቱ ላይ የመበታተን አደጋ እንዳይከተል ለመከላከል ብልህነትና ጥበብ የተሞላበት አካሄድን መከተል የሚጠይቅ ጉዳይ መሆኑ ትኩረት ሊሰጥው የሚገባ ጉዳይ ነው። ስለዚህ የአገር መከላከያ ኃይል ታማኝ መሆን ያለበት ላገር ሉዓላውነት እንጂ ለአንድ ወይም ለሌላ የፖለቲካ ድርጅት እንዳልሆነ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ሕዝባዊ (ሲቪክ) ማሕበራት ደጋግመው ማስተማር አለባቸው።

ይህ ፀሐፊ ኣንዳንድ የፖለቲካ ቡድኖችና አክራሪ ግለሰቦች እንደሚሉት እገሌ ከዚህ ብሔር የመጣ ጀኔራል፣ ኰለኔል፣ መቶ አለቃ ….. ወዘተ የሚል ዝርዝር ውስጥ የመግባት አባዜ የለውም። ችግሩ ያለው ጀኔራሉ የወጣበት የብሔረ-ሰብ ማንነት ላይ ነው የሚል እምነትም የለውም። የችግሩ መሠረታዊ መንስኤ ከጀኔራሉና ኰሌነሉ የፖለቲካ አቋም ወይም አድር-ባይ ባሕሪ የሚመነጭ ነው። ስለሆነም ግለሰቦቹ የወጡበት ብሔረ-ሰብ ጋር ለማገናኘት መሞከሩ ረጅም መንገድ የሚያስኬድ አይሆንም። አምባገነን አገዛዞች እስካሉ ድረስ ቁልፍ ቦታን የሚሰጡት ለታማኝ አገልጋያቸው መሆኑ ድሮም የሚታወቅና የነበረ እንጂ ዛሬ በህወሓት/ኢህአዴግ ቁንጮዎች የተጀመረ አይደለም። አምባገነናዊ አገዛዝ እስከቀጠለም ዛሬም ሆነ ነገ የሚቀጥል እንጂ የሚቆም አይሆንም። ዛሬ የሚሾመው የሚሸለመው የትግራይ ተወላጅም ከሆነ ያን መዓርግ የሚያገኘው በትግራዊነቱ ሳይሆን፣ ለአምባገነኑና አምባገነኑ ሊያስፈጽማቸው ለሚያቅዳቸው ዕቅዶች ምቹ ሆኖ በመገኘቱ ብቻ ነው ሊሆን የሚችለው። ለአምባገነኖቹ ተውኔት አንምበረከክም ያሉት እነ ጀኔራል ጻድቃን ገ/ትንሳኤ፣ ጀኔራል አበበ ተ/ሃይማኖት፣ ጀኔራል ታደሰ…. ወዘተ ከሥልጣን እንዲባረሩ የተደረጉት ከሳሞራ የኑስና መሰል አድርባ መኰንኖች ያነሱ ትግራያዊያን ስለሆኑ አይደለም። ከሠራዊቱ አመራርነት የተወገዱት የአቶ መለስን ፍላጎት ለመፈጸምና ለማስፈጸም ምቹ ሆነው ባለመገኘታቸው ብቻ ነው። የነአቶ መለስን ፍላጎት ያለ ምንም ጥያቄ ለሚፈጽምና ለሚያስፈጽም ሁሉ የሥራ ቦታው ክፍት መሆኑ መጠርጠር የለበትም። አሁን የወታደሩን ሥልጣን የያዙት በብዛት የትግራይ ተወላጆች ቢሆኑ፣ ያን ሥልጣን ያገኙት በትግራያዊነታቸው ሳይሆን ለአገዛዙ ባላቸው ታማኝነት ብቻ እንደሆነ ከላይ እንደ አብነት የተጠቀሱ ጀኔራሎችን ማጣቀስ ይቻላል። ስለሆነም፣ ፍትሓዊ ያልሆነ አሠራር ካለ ከየትም ብሔር ይወለድ ከየት አሠራሩ መስተካከል አለበት ብሎ ይህ ፀሐፊ ያምናል። ከዚህ ብሔር ወይም ከዛኛው ብሔር የወጣ ነው! የሚለው አባባል ግን ከህወሓት/ኢህአዴግ አባባልና ተግባር ተለይቶ የሚታይ አይሆንም።

አሁን ባለው መልኩ ሲቃኝ፣ የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት እንደ ተቋም የኢህአዴግ አመራሮች ጉዳይ አስፈጻሚ ነው ሊባል የሚቻል ነው። ይህ የሆነው ግን ከትግራይ የሚወለዱ ወታደራዊ መኰንኖች ተቋሙ ውስጥ ቁልፍ ቦታ በብዛት ስለያዙ ሳይሆን ተቋሙ እንደተቋም ከህወሓት/ኢህአዴግ ፖለቲካ ጋር በቀጥታ የተቆራኘና የአምባገነኖች መጠቀምያ እንዲሆን ተደርጎ የተዋረቀ በመሆኑ ነው። ባጠቃላይ የተቋሙ አወቃቀር እስካልተስተካከለ ድረስ ከፈለገው ብሔረ-ሰብ ይምጣ እዛ ተቋም ውስጥ የሚያገለግል ወታደራዊ መኰንን ሌላ የተሻለ ሥራ ይሠራል ወይም ህዝባዊ ወገን ይሆናል ብሎ መጠበቅ የሚቻል አይሆንም። ይህ ማለት አንዳንድ ህዝባዊ አመለካከት ያላቸው መኰንኖች አይኖሩም ማለት እንዳልሆነ ግን ልብ ሊባል ይገባል። አሁን ካሉት መኰንኖች ውስጥ የተወሰኑም ቢሆኑ ሁኔታው ባይፈቅድላቸው እንጂ ህዝብን የሚወግኑ ሊኖሩ እንደሚችሉ ጥርጥር የለውም። ከየትም ይምጡ ከየተኛው ብሔረ-ሰብ አሁን ቁልፍ ቦታን የያዙ ጀኔራሎች አብዛኞቹ ተጠሪነታቸው ኢህአዴግ ለሚመራው መንግሥት መሆኑ ግልጽ ነው። ለምሳሌ የማይሆነውን እንደሚሆን አድርገን በማሰብ ኢህአዴግ በምርጫ በዝረራ ተሸንፎ ሌላ ፓርቲ ሥልጣን ቢጨብጥ ይህ ሠራዊት አሁን ባለው መዋቅር ውስጥ ሆኖ የመንግሥትነት ሥልጣን

ለሚረከበው ሌላ ፓርቲ ታዛዥ ሆኖ የመቀጠሉ ጉዳይ ቢያንስ ያጠራጥራል። ይህ ጥርጣሬን የሚያጠናክር መነሻም አለ።

ይኸውም፤ የዛሬቱ ኢትዮጵያ የአገር መከላከያ ሠራዊት ከአመጣጡ የአንድ ግንባር ማለት የህወሓት/ኢህአዴግ ፖለቲካዊ አመለካከትና አቋም ላይ ተመሥርቶ ከድርጅት ሠራዊትነት በአዋጅ ወደ አገር መከላከያነት የተሸጋገረ ኃይል መሆኑ እንደ ምክንያት ሊጠቀሱ ከሚችሉ ነጥቦች ውስጥ አንዱ ነው። በመሆኑም በዚህ ዓይነት መንገድ ተፀንሶ በአዋጅ ብቻ ወደ አገር መከላከያነት ተሸጋግሮ የተደራጀ መከላከያ ሠራዊት ላቋቋመው አካል ካለው ታማኝነት ተላቆ እንዲሁ በአዋጁ መሠረት፤ ባንዴ ገለልተኛ ሆኖ ሊገኝ ይችላል ብሎ ማሰብ ቢያስቸግርም፤ አይሆንም ተብሎ ተስፋ የሚቆረጥበትም አይደለም። በ20 ዓመታት ውስጥ ከራሱ ከሠራዊቱ ጀምሮ ባጠቃላዩ ሕብረተ-ሰብ ውስጥ የተንሰራፋውን የፍትሕ መጓደልና የደረሰው የኑሮ ምስቅልቅልን በተጨባጭ ለመገንዘብ አስችለውት እንደሚሆኑ ጥርጥር የለውም። በመሆኑም ከተሰራበት የሚነሳው ህዝባዊ አመጽን ደግፎ ለመሰለፍ የማይችልበት ሁኔታ ስለሌለ ወገናዊነታችንን ልናሳየው ይገባል። ይህ ሠራዊት ለዓመታት የማሌሊት/ ህወሓት ርእዮተ-ዓለም ተግቶ፤ በዛ ተኰትኵቶና ተጠምቆ ያደገ ሠራዊት ቢሆንም፤ ሲነገረው የነበረና ሥልጣን ከተያዘ በኋላ ያለው አካሄድ ምን እንደሚመስል በተጨባጭ አይቷል። ስለሆነም፤ ተራው ወታደርና የበታች መኮንኖችን ለአምባገነኖች የሥልጣን ጊዜን ለማራዘም ከሚሠሩ ታማኝ ባለ ከፍተኛ መዓርግ መኮንኖች መለየትን እንደቀዳሚ ተግባር ተደርጎ መወሰድ አለበት። አምባገነን ገዢዎቹ፤ ከዚህ በፊት በየጊዜው የተቀሰቀሱ የተማሪዎችና የህዝቡ ሰላማዊ አመፆችን ለማክሸፍ የተጠቀሙት በወታደራዊ ኃይል መሆኑና በዚሁ መንገድ ከመቀጠልም እንደማይቆጠቡ መታወቅ አለበት። የኢህአዴግ አምባገነን መሪዎችን ፍላጎት ለማስፈጸም በሚያስችል መልኩ የተዋቀረ ተቋም ዞሮ ዞሮ የሚያስጠብቀው የነሱን ጥቅም መሆኑ ግልጽ ነው። የአንድን አገር ሠራዊት ተቋማዊ አወቃቀር ከፖለቲካ ድርጅት ጥገኝነት አውጥቶ ገለልተኛ ሆኖ ተጠሪነቱ ለአገሪቱ ሕገ-መንግሥት ብቻ እንዲሆን ተደረጎ መደራጀት ይኖርበታል። የኢህአዴግ መሪዎች ይህንን ለማድረግ ዝግጁ አይደሉም። ከዚህ በፊት ተጠሪነታችን ለአገሪቱ ሕገ-መንግሥት ነው ያሉት ጀኔራሎች ከነበራቸው ኃላፊነት እንዲወገዱ የተደረገውም በዚህ ምክንያት ነው። አሁን የምናየው የመከላከያ ተቋም የህወሓት/ኢህአዴግ መሪዎችን የሥልጣን ዘመን ለማርዘም በሚያመች መልኩ የተዋቀረ መሆኑ ግልጽ ነው። የ1997 ዓ.ም. ምርጫን ተከትሎ የተነሳው ሰላማዊ ህዝባዊ ዓመፅን ለማስቆም የአቶ መለስ ሠራዊቱን መጠቀማቸው የሚያሳየን ይህንን ሐቅ ነው። ከዚህም በመነሳት አሁን ባለው መልኩ ሲታይ፤ የአገር መከላከያ ተቋም ኢህአዴግን ከኢትዮጵያ በላይ አድርጎ እንዲመለከት ተደርጎ የተዋቀረ ነው ቢባል የተጋነነ አይሆንም። ስለሆነም፤ አሁንም ሰላማዊ ህዝባዊ አመጽ ሲነሳ የአገር መከላከያ ሠራዊቱ የአቶ መለስ ዜናዊ ዱላ ሆኖ እንዳያገለግል ማስተማርና መቀስቀስ ያስፈልጋል።

ሕብረተ-ሰቡን ጠላትና ወዳጅ በማለት በሁለት ከፍሎ ሠራዊቱን ሌት ተቀን "በአብዮታዊ ዴሞክራሲ" ርእዮተ ዓለም እንዲታነጽ የሚደረገውም ለግንባሩ መሪዎች በዱላነት እንዲያገለግል ታስቦ ነው። ጥያቄ ያነሳ "በግምገማም" ስም የሚዋከብበት፤ የሚታሰርበትና የሚባረርበት ሁኔታ እየተከሰተ የምናየውም ለዚህ አገልግሎት ለማመቻቸት እንደሆነ ግልጽ ነው። ይህንን ለማክሸፍ ከተፈለገ ሠራዊቱ ውስጥ ከፍተኛና ቀጣይነት ያለው ሥራ መሠራት ይኖርበታል። አሁን ያለን የአገር መከላከያ ሠራዊት አገሪቱን የመከላከል ተልእኮውን የመወጣት ብቃት ያለው መሆኑ ቢታወቅም፤ የሠራዊቱ አመራር የኢትዮጵያን ህልውናን የሚመለከተው ከጠባብ የህወሓት/ኢህአዴግ ርእዮተ-ዓለምና ፕሮግራም አንጻር መሆኑ ግልጽ መሆን አለበት። የአገር መከላከያ ሠራዊት ውስጥ ቁልፍ ቦታ ለማግኘት ለሕወሓት/ኢህአዴግና ለሚከተለው "የአብዮታዊ ዴሞክራሲ" ርእዮተ-ዓለም

ያለህ ታማኝነት መቶ በመቶ መረጋገጥ እንዳለበት የታወቀ ነው። በዚህ በኩል ያለውን ፈተና ያላለፈ ለወታደራዊ ሥልጣን ሊታጭ የማይቻል ነው። ተሹመህም የአቶ መለስን ፍላጎትና ምኞት ካላሟላህ በዜግነትህ ልታገኘው የሚገባህን የሓላፊነት ቦታ የፈለገው ብቃትም ቢኖርህ፣ ይዘህ ለመቆየት አይቻልም። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም ባስፈላጊው መንገድ ሊወገድ እንደሚችል ያውቀዋል። ከዚህ የተነሳ የእያንዳንዱ ጀኔራል ውስጣዊ ፖለቲካዊ አቋም ምን ሊሆን እንደሚችል ለመገመት አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። ሆኖም፣ የዛሬው የአገር መከላከያ ውስጥ ቁልፍ ቦታ የያዙ ጀኔራል፣ ኰለኔል ወዘተ. ከሰላማዊ ህዝባዊ ንቅናቄ ጐን ማሰለፍ ቀላል አይሆንም። ይሁን እንጂ መሰራት ያለበት ሥራ በመኮንኖቹ ውስጥም በተለይ ደግሞ በሠራዊቱ ውሰጥ ያለማቋረጥ መሠራት የግድ ነው።

በተለይ ጭቁኑንና ህዝባዊ ወገን ሊሆን የሚችለውን የብዙኃኑን የሠራዊቱ አባላት የሰላማዊ ህዝባዊ ዓመፅ አጋር እንዲሆኑ የማድረግ ሥራ በሚገባ ከተሰራ በርካታዎቹን የሰራዊቱ አባላት ከህዝባዊ አመጹ ጎን ለማሰለፍ የሚቻልበት ሁኔታ ተፈጥሮ  የድሉን ቀን ለማቀላጠፍ ይቻላል። ካልሆነም ሠራዊቱ በህዝባዊ አመጹ ላይ ሊያነሳው የሚችለውን ዱላ እንዳያነሳ በማስደረግ የሚከፈለውን መስዋዕትነት እጅጉን ለመቀነስ እንደሚያስችል በመገንዘብ ተገቢ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። ይህን ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ የተወሰነ ጊዜ ያስፈልጋል። አቶ መለስና ድርጅታቸው ሥልጣኑን በህዝብ ፍላጎት እንደማይለቁ የታወቀ ነው። ስለሆነም ህዝባዊ አመፁ አይቀሬ እንደሆነ በመረዳት፣ ይህ የሚነሳው ህዝባዊ አመፅ በድል እንዲጠናቀቅ ሠራዊቱ ውስጥ ሰፊ ሥራ መሰራት ይኖርበታል። አጠቃላይ ህዝቡን የማደራጀት ሥራም በስፋት መሠራት ይኖርበታል። የአገር ቤትና የውጪ ትግል በሚገባ መቀናጀት ይኖርበታል። በመሆኑም፣ አስፈላጊ ጊዜ ወስዶ ተገቢ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ጠቃሚ ነው። ህዝባዊ አመፅ ሲነሳ አቶ መለስ ወታደራዊ እርምጃ እንደሚወስዱ ከወዲሁ ስለሚታወቅ፣ አስቀድሞ ጀኔራሎቹን ከበታች የሠራዊቱ አባል ለመለየት መቻል አለበት። የሆነ ለውጥ ቢመጣም ወታደሩ የአገር መከላከያ ኃይል ሆኖ እንደሚቀጥልም ዋስትና ሊሰጠው ይገባል።

መጋቢት 23 ቀን 2003 ዓ.ም